# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 28

ነሐሴ 22 ቀን 2014ዓም(28-08-2022)

ያገራችን ነገር ውሃን ቢወቅጡት እምቡጭ እዬሆነ፣በችግር ላይ ችግር እዬተደራረበ የሄደበት ሰሞን ነው።የሕዝቡ መከራ፣የአገራችን የመበታተን አደጋ ይበልጥ እያደገ እንጂ እዬተወገደ አልመጣም።ለአገር አንድነት ይቆማሉ የተባሉት ማህበረሰቦችን በሆነ ባልሆነው እያዳከሙ የመሄዱ ተግባር መጠኑ ጨምሯል።በሰላም ኑሮዬን ልግፋ፣በዋና ከተማዬ ገብቼ ኑሮዬን ልመስርት ወይም ዘመድ ጠይቄ ልምጣ፣ላደረብኝ በሽታና ሕመም በተሻለ መንገድ የሃኪም እርዳታ ወዳለበት ያገሬ ዋና ከተማ ገብቼ ላግኝ፣በሰላም ኑሬ ሠርቼ ያፈራሁትን ንብረት ተዘርፌ፣ከዬክልሉ አሸባሪዎች ጭፍጨፋ አምልጬ ተፈናቅዬ ሜዳ ላይ በመፍሰሴ ፍትሕ ይሰጠኝ፣አገር መውደድ ሃጢያት አይደለም ! ብሎ የሚጮኸው ዜጋ ዛሬም ድምጹ አልተሰማለትም፤እንደወንጀለኛም መጠለያ አይሉት እስር ቤት ውስጥ ታጉሮ፣ ዙሪያው ገደል ሆኖበት በስቃይ አለንጋ ይገረፋል።ሁሉም ብሶት አለበት፣ሃኪሙ፣መምህሩ፣ነጋዴው፣ ተማሪው፣ ወጣቱ፣አርሶ አደሩ---ወዘተ ጥያቄ ቢያቀርብም ሰሚ አላገኘም።ይባስ ብሎ በመንግሥት ሃይል እዬተደበደበና እዬታፈሰ በመከራ ላይ መከራ እያስተናገደ ነው።

ለመከራው ሁሉ ተጠያቂ የሆነ መንግሥት ነኝ ባይ ቡድን አገርን ለማፈራረስ እንጂ የሕዝቡን ሙብትና ነጻነት ብሎም ሰላም ያስከብራል ተብሎ አይጠበቅም።ይባስ ብሎ የሚያደርገውን አገር የመናድ ዓላማ በአገሪቱ መናገሻ ከተማ በሆነችው በአዲስ አበባ ጀምሮታል።ይህንንም እንደ አንዱና ዋናው የተሳካ ተግባር ሲል የሥርዓቱ ተጠሪ የሆነው አብይ አህመድ በኩራትና በእብሪት የብልጽግና የወጣት ክንፍ የሆነውን ጀሌ በቤተመንግሥቱ ሰብስቦ ዲስኩር በሰጠበት ወቅት ገልጾታል።ይህንኑ የአገር የማፍረሱ ፕሮጀክት አካል የሆነውን የአዲስ አበባን ክፍለከተማዎች የመዋጥ እርምጃ በሕዝቡ ፈቃድና እውቅና ሳይሆን በባለተረኞቹ የኦሕዴድ ባለሥልጣኖች የተከናወነ በመሆኑ በማይታጠፍ መልኩ ትልቁና ወሳኙን ግባችንን አጠናቀናል (Hoera! Mission Accomplished)በማለት ሲመጻደቁበት አይተናል፤ ሰምተናል።በዚህም አላቆመም በከተማዋ በሚገኙ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች የኦሮሚያ ቋንቋን በግድ ለማስተማር ዕቅዱ መውጣቱንና ተግባራዊ መሆኑን ፣ባልሆኑበትም ትምህርት ቤቶች በቅርቡ ተግባራዊ እንደሚሆን የተረኛው ቡድን የትምህርት ጉዳይ ባለሥልጣን የሆነው በድፍረት ይፋ አድርጓል።ይህንን ተከትሎ በከተማዋ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችና መምህራን እንዲሁም ወላጆችና የከባቢው ነዋሪዎች የተቃውሞ ድምጻቸውን እያሰሙና አሻፈረን በማለት ከትምህርት ቤት መውጣታቸው በቦታው የተገኙ ጋዜጠኞች ዘግበዋል።ይህም ሆኖ ግን የእብሪተኛውን የኦሮሙማ ቡድን ውሳኔ ሊቀለብሰው አልቻለም።ምክንያቱም የሕዝቡ ትግል የተቀናጀና በአንድ ብሔራዊ አስተባባሪ አካል ስላልተመራ ነው።ያንን የሕዝብ ትግል የሚያስተባብር የተደራጀ የትግል አካል ይፈጠር ፣ካለም ጊዜው አሁን ነው እንላለን።ተበታትኖ በዬተራ መጠቃቱና መጮሁ መፍትሔ አይደለምና ሰብሰብ ያለ ሕዝባዊ ሃይል መፍጠሩ የግድ ይላል።

ለተረኛው የኦሮሙማ ዓላማ ውለታ የዋለችው የከተማዋ ከንቲባ አዳነች አቤቤም ለከፍተኛ የሚንስቴርነት ሹመት እንደታጨችና የያዘችውን ቦታ ለመልቀቅ ለይስሙላ ደብዳቤ እንዳስገባች ሰምተናል።ከሷ በፊት የነበረውም ታከለ ኡማ የኦሕዴድን ፍላጎት ሲንከባከብና ሲያስከብር፣የከተማዋን ቦታ ሲቸበችብ ላደረገው ውለታና ባካበተው የሌብነት ችሎታና ልምድ ከከንቲባነት ብዙ ዘረፋ ሊያካሂድ ወደሚችልበት የማእድን ሚንስቴርነት ቦታ መብቃቱን የምናውቀው ነው።የአዳነች አቤቤም ተከታይ ሹመት ከዚያ ያላነሰ ምናልባትም ታከለ ኡማ በህመምና በእረፍትም ሽፋን ከአገር በመውጣቱ

ሳይመለስ ከቻለ በሌላም በኩል የሚነፍሰው ወሬ እንደሚያመለክተው በስርቆት መወንጀሉን ፈርቶ ሸሽቶ መሄዱን ጭምጭምታ መኖሩን ተከትሎ መንግሥት ከክስ ነጻ መሆኑን ስላረጋገጠለት ሳይመለስ እንዳልቀረ የሚመስል ወሬ ይሰማል፤ተመለሰም አልተመለሰም፣ ግራም ነፈሰ ቀኝ አዳነች አቤቤ የታከለም ሆነ ሌላ የዘረፋ ቦታ ላለመረከብ የሚያግዳት የለም።እሷም እንደ ታከለ ኡማ ብዙ ልምድ ያካበተች፣በጉምሩክ ባሳዬችው የሌብነትና ተረኝነት ሙያዋ፣በአቃቤ ሕግነቷ ለኦሕዴድ ያላትን ታማኝነት በማረጋገጧ ለከንቲባነት በቅታለች።ለሌላም ከፍተኛ ቦታ መታጨቷ አያስገርምም። ጥያቄው የሷን ቦታ ማን ይተካ ይሆን ? የሚለው ነው።በአብይ አህመድ የማጭበርበር ስሌት ለአንድ ሹመት የግድ የኦሕዴድ አባል መሆን አይጠበቅም፤ እንደውም ሃሜታውንና ጥርጣሬውን ለመቀነስ ሲባል ከሌሎቹ ድርጅቶች ግን ከኦሕዴድ በላይ ኦሕድድ የሆነ ሰው መሳይ ፈረስ መመደቡ አይቀርም እንላለን።በተከታታይ የታዬውም ይኸው ነው።ምክትሏ ጃንጥራርም ቢሆን ያው የአማራው ኦሕዴድ ነው።ማንም ቢሆን በዚህ ሥርዓት ውስጥ አገልጋይ ከሆነ የጎሳ ማንነቱ ከጥያቄ ውስጥ አይገባም። ደመቀስ ቢሆን አገኘሁ ተሻገር ወይም ተመስገን ጥሩነህና መሰሎቻቸው አማራነታቸው መች የኦሕዴድ -ኦነግ ምርኩዝ ከመሆን አገዳቸው?

ስለአዲስ አበባና ነዋሪው ሕዝብ የሚከራከረውን ባልደራስን በጠራራ ፀሐይ ኩዴታ አዘጋጅተው መሪው እስክንድር ነጋና ተባባሪዎቹ የገቡበት አልታወቀም።እስከአሁን ድረስ መልስ ያላገኘ ምስጢር ሆኗል።እስክንድር ነጋን የበላው ጅብም አልጮኸም።በጣም የሚያስተዛዝበው ነገር ስለእስክንድርና ታዲዮስ ታንቱ፣ስለተመስገን ደሳለኝና ስንታዬሁ ቸኮል እንዲሁም ስለቀሩት ይጮሁ የነበሩት ጋዜጠኞም ሆኑ ዩቲዩበሮች በአሁኑ ጊዜ ውሾን ያነሳ ውሾ ይሁን ያሉ ይመስል ድምጻቸውን ከማሰማት ገሸሽ ማለታቸው ነው።የሴራው አካል ይሁኑ ወይም ግራ ተጋብተው ይሁን የሚታወቅ የለም፤ጊዜ ሁሉንም ያሳዬናል።የሚያስተዛዝበው ቢኖር እንዳለመታደል ሆኖ ደፋርና ጀግና መሪዎችን እያስበሉና አሳልፈው እዬሰጡ የመሪ ያለህ የሚል ጩኸት ማሰማቱ ነው።ጀግና ከሞተ በኋላ የሚያወድስ ፣በቁሙ የሚወቅስ ማህበረሰብ መሆኑ በራሱ የተፈጥሮ ድካም ያለበት ይመስላል።

የአዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝብ ያልመረጥኩት ሰው ከንቲባ አይሆንብኝም ብሎ ቢነሳና ምርጫ ማካሄዱ የግድ ቢሆን ስለ አዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝብ የሚከራከረውን ባልደራስን ይመርጣል ብሎ ስለሚፈራ በቅድሚያ ባልደራስን ማዳከምና መሪዎቹን ማሶገድ ቀላሉ ዘዴ ይሆናል።ለቀጣዩ የኦሕዴድ ሹመኛ የማመቻቸት ሥራ ነው ብለን እንገምታለን።የአዲስ አበባ ሕዝብ ይህንን ከግምት ውስጥ አስገብቶ እንዳለፉት ጊዜያቶች በዝምታና በፍርሃት ድባብ ተውጦ ሥልጣን ላይ ለወጡት አገር አጥፊዎች መጫወቻነቱን ላንዴም ለሁሌዬውም እምቢ ብሎ የራሱን ከንቲባ ለመሾም መታገል አለበት፤መብቱን በትግሉ እንጂ በልመና የሚያገኘው አይደለም።እራሱ ይምረጥ ስንልም በሰርጎ ገቦችና በመንግሥት ተብዬው ቡድን በሚመራ የምርጫ ሂደት እንዳይወናበድ የሚያምነው አካል ምርጫውን እንዲያዘጋጀውና እንዲታዘበው ማድረግ ይኖርበታል።የአዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝብ የራሱ ከተማ ባለቤት ከሆነ በቀጣዩ የአገሩ የኢትዮጵያ ባለቤት ለመሆን አይሳነውም።የሱ ድል ለሌላው ወገኑ የማንቂያ ደወልና ፊትአውራሪ ነው።መናገሻ ከተማዎች ለአገራዊ ለውጥ ግንባር ቀደም ሚና እንዳላቸው ባለፈው ዘገባችን የገለጽነው ቢሆንም ዛሬም እንደግመዋለን።አዲስ አበቤዎችም እንደሌሎቹ አገሮች ዋና ከተማ ነዋሪዎች የለውጥ ሞተር ከመሆን የሚያግዳቸው አይኖርም።ለመሆንም በእጃችሁ ያለውን የሞተሩን ቁልፍ ተጠቀሙበት እንላለን።በወታደራዊ ዘመቻም ሆነ በፖለቲካ ትግል ወሳኝ የሚሆነው የስበት ማእከል (Center of Gravity)የሆነውን ቦታ መቆጣጠር ነው።አዲስ አበባም የአገሪቱ የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚ፣የዲፕሎማሲና የተለያዩ ተቋማት እምብርት ስለሆነች ነዋሪው ሕዝብ ታግሎ የከተማዋን ሥልጣን በእጁ ካደረገ ቀሪው የአገሪቱ ክፍል ፈለጉን ተከትሎ ለውጡ አገር አቀፍ መልክ ይኖረዋል። ጠላትም ዋና መቀመጫውን ከተነጠቀ እንደ ዱቄት ይበተናል ወይም እንደ እምቧይ ካብ ይናዳል።

ለይምሰል ይሁን ለማጭበርበር የባልደራስ አመራር ነኝ የሚለው ስብስብ አባላቱን በመጥራት ስብሰባ ለማካሄድ ሞክሮ በፖሊስ ሃይል መታገዱና አዳራሹ መከበቡን ለመስማት ችለናል።ከመንግሥት ጋር አታካሮ የገጠመ ለማስመሰል ከሆነም እያደር የሚታወቅ ይሆናል።

ከአዲስ አበባ ወጥተን ወደ ጎጃም ብር ሸለቆ ስናመራ በአማራ ክልል ውስጥ በመንግሥት እውቅና የልዩ ሃይል አባላት የሚሰለጥኑበትን ጣቢያ እናገኛለን። በዚህ ጣቢያ በመሰልጠን ላይ ያሉትን የልዩ ሃይል አባላት በአማራነታቸው ከፋኖ ጋር ይደባለቃሉ፣ወይም የኦነግን መስፋፋት ያግዳሉ የሚል ስጋት ያደረበት የአብይ አህመድ መንግሥት ከምስለኔዎቹ ከክልሉ አመራሮች ጋር በመመሳጠር በመከላከያ ሚኒስትር ተብዬው በብርሃኑ ጁላ ትእዛዝ ከበባ ተደርጎ ብዙ ሰልጣኞችና  እስከ ጄነራል ማዕረግ የደረሱ አመራሮችና የመስመር መኮንኖች መገደላቸውና መቁሰላቸው ይፋ ሆኗል።በዚሁ በአማራው ክልል ባለሥልጣናት ትእዛዝ ከ15 ሺህ በላይ የፋኖ አባላትና ደጋፊዎች በእስር ቤት በመማቀቅ ላይ ይገኛሉ።ላለፉት ዓመታት ግን  በኦሮሚያ ክልል እስከ 43 ዙር ከ150 ሺህ በላይ የሚሆን ልዩ ሃይል እንደ አሸን ሲፈላ ያም በኦሕዴድ-ኦነግ የእድገትና  የጀግንነት ኩራት ሆኖ ሲወደስና ሽፋን ሲሰጠው፣ በአማራው ክልል ውስጥ ግን የልዩ ሃይል ማሰልጠኑና ማደራጀቱ እንደ ወንጀል ይቆጠራል።ሕዝባዊ ጦር በጎሳ ተዋረድ መቋቋሙን ብንጠላውም፣ለአንዱ ጎሳ መብት ሆኖ ሲፈቀድ ለሌላው ወንጀል የሚሆንበት ሕጋዊ መሰረት የለውም።በተለይም በአማራው ላይ ሲሆን መጠንከሩ ካለው ኢትዮጵያዊነት መንፈስ ጋር ከተደራጀ አገር ለማፈራረስ ዕድል አይኖረንም ከሚል ስጋት የተነሳ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም።

አማራውን በማዳከሙ ዘመቻ ከመከላከያ ጦሩ ጎን ለጎንም የኦነግ አሸባሪ ቡድን የተባበረ መሆኑን በቦታው የነበሩና ተማርከው የተያዙት መስክረዋል።ኦሕዴድና ኦነግ መተባበራቸው እንግዳና አዲስ ነገር አይደለም፣ከአባትና ልጅ ግንኙነት የሚጠበቅ ነው ።ለጋራ ዓላማቸው የጋራ ጠላት በሆነው በአማራው ላይ ተባብረው እንደሚቆሙ ሳይታለም የተፈታ ነው።ይህ አንድነታቸውን የገለጹበት በዘመቻም በመመሪያም የአብሮነታቸው ማሳያ ነው።

የብዙ መከራ ሰለባ የሆነው የአማራው ማህበረሰብ ብሶቱ ገንፍሎ ለመደራጀት ሲነሳ ከውስጥም ከውጭም ጠላቶች ተነስተው እንደሚረባረቡበት በግልጽ ያዬንበት ሰሞን ነው።በትረመንግሥቱን በጉልበትና በሴራ የጨበጠው የኦሮሙማው ቡድን የሚያደርሰው ጥቃት እንዳለ ሆኖ በአማራው ስም የተቋቋሙት ስብስቦች በሌላ በኩል ሆነው ተመሳሳይ ችግር እዬፈጠሩበት መሆኑን ታዝበናል።ገና ከጧቱ ጀምሮ ጸረ አማራነቱን ያሳዬውን ብአዴንን ወደ ጎን ትተን ከሶስት ዓመታት ወዲህ ብቅ ያለውን ጥጃ ድርጅት አብንን(አማራ ብሔራዊ ንቅናቄ)ስንፈትሸው በንትርክና በውዝግብ የተነከረ ከመሆን አልፎ መሪዎቹ በሹመትና ሽልማት ካለው ገዢ የኦሮሙማው ቡድን ጋር ተመሳጥረው ቆመንለታል ያሉትን ሕዝብ ከድተው እንደቆሙ ታዝበናል።የፋኖን አገር ወዳድ ሃይል ለማዳከም መንግሥት ያወጣውን መመሪያና ዘመቻ በመደገፍ፣አለያም አስታራቂ ሽማግሌ በመሆን ትጥቁን እንዲፈታ ለማድረግ መሰለፋቸውን በቦታው ከዋሉት ከአብን አመራር አንዱ ከሆነው ከክርስቲያን ታደለ አንደበት ሰምተናል።ክርስቲያን ታደለ እንደገለጸው ከሆነ፣-ፋኖ  የአንድ ግለሰብ ጭፍራ ስብስብ ሽፍታ ይመስል በምህረት ጠብመንጃ እንዲያወርድ  በዬስብሰባውና በአብይ አህመድ ፈቃድና ፍላጎት መኖሩን በመግለጽ ለግለሰቦች  የክልሉ ምስለኔ ቡድን ምህረት እንዲያደርግ መስማማቱንና የፋኖ መሪዎች የተባሉትም መቀበላቸውን ክርስቲያን ታደለ ገልጿል።ለመሆኑ ዓላማ ሰንቆ ለትግል የወጣ ይቅርታ ተደርጎልሃልና ግባ ቢሉት እሺ ብሎ ይቀበላል?ከተቀበለስ ጫካ የገባውና መሣሪያ ያነሳው ለመታወቅና በይቅርታ ድርድር ለሹመት ለመታጨት ነው?ይህንን የሽምግልና ጥሪ የተቀበሉ ፋኖዎች ካሉ መልስ ይስጡበት።በእኛ ግንዛቤ ግን ፋኖ ብለን የምንጠራው ለሃገሩና ለወገኑ ክብርና መብት ዓላማ ሰንቆ

ህይወቱን ለመገበር ታጥቆ የተነሳን እንጂ፣እታገለዋለሁ ለሚለው አካል እውቅና ሰጥቶ ለሚያቀርበው የምህረት ጥሪ እጁን የሚሰጥ አይደለም።ለድርድር ብሎ ጫካ ገብቶ የሚመለስ አስመሳይ ቡድንና ግለሰብ በእኛ በኩል ፋኖ ነው አንልም። ፋኖ ስንልም በጥቅል መጠሪያ ሕዝባዊ ጦር ማለት እንጂ መሣሪያ ተሸክሞ ጸጉሩን አበጥሮ የሚንጎባለል የከተማ አውደልዳይ አይደለም።ፋኖነት አገርና ሕዝብ ሲታመስና በጠላት ሲደፈር እምቢ ላገሬ፣እምቢ ለወገኔ ብሎ ከመደበኛ ሥራው ተነጥሎ ህይወቱን ገብሮ አገርና ወገኑን ለማዳን የተሰለፈ ሕዝባዊ ሠራዊት ማለት ነው።ይህንንም ከወያኔና ከኦነግ ወራሪ ሃይል ጋር በተደረገ ተደጋጋሚ ጦርነቶች አሳይቷል፤ አሁንም በማሳዬት ላይ ነው። የፋኖ ጦር የብዙሃን ስብስብና በብዙሃኑ በተመረጠ አመራር ፣ድርጅታዊ ሰንሰለት ያለው የተደራጀ ጦር እንጂ በአጃቢ የተከበበ ግለሰብ ማለት አይደለም። በግለሰቦቹ፣ፈቃድና ፍላጎት የሚንቀሳቀስ ከሆነ እጣ ፈንታው የግለሰቦቹን ፍላጎትና እጣ ፈንታ የተከተለ፣ህይወቱም በመኖራቸውና ባለመኖራቸው ምክንያት ይወሰናል ማለት ነው።መሪው እጁን ቢሰጥ ወይም በአደጋ ቢነጠል ይበታተናል ማለት ነው።ድርጅታዊ መዋቅር ያለው ከሆነ ግን ክፍተቱን እዬሞላ እስከ ድል ድረስ ይዘልቃል።ለዚያ ድል እንዲበቃ ድርጅታዊ ቁመና ይኑረው እንላለን።

ባለፈው ዘገባችን ያነሳነው ሌላው ጉዳይ የወያኔና ኦሕዴድ አገር አጥፊ ቡድን በሥልጣን ሽኩቻ ምክንያት አገራችንን የጦር አውድማ እንዳደረጉና ያንንም ከይሲ ዓላማ ለማስፈጸም ጎራ ለይተው የፈረደበትን ሕዝብ አሳስተውና አስገድደው በጦር ሜዳ ማግደው የአሞራ ሲሳይ እንዳደረጉት የዓለም ሕዝብ የታዘበውና የመዘገበው አሳፋሪ ታሪክ ነው።ይህም አገር የማፈራረስ ዓላማ ያለው ጦርነት የውጭ ሃይሎች ገብተው እንዲያቦኩበት ዕድል ፈጥሮላቸዋል።አገራችን የመሣሪያና የፖለቲካ ቤተሙከራ ሆናለች።ጎራ በለዩ ታላላቅ አገሮች ጥርስ ውስጥ ገብታ እዬደቀቀች ነው።ወያኔን ተገን ያደረገው አሜሪካ መራሹ ጎራ በአንድ በኩል፣በሥልጣን ላይ ያለውን ኦህዴድ መራሹን ቡድን ደግፈው በሩስያና ቻይና ጥላሥር የተሰለፉ ጸረ ምዕራባዊያን የሆኑ አገሮች በሌላው ጎራ ሆነው ደሃው የኢትዮጵያ ሕዝብ የመስዋዕት በግ እንዲሆን ተፈርዶበታል።ከሁለት ዓመት በፊት በተደረገው የሥልጣን ጦርነት ሳቢያ ከ500 ሽህ ሰው በላይ ህይወቱን እንዳጣና አካለጎደሎ እንደሆነ ይገመታል።ከጦርነቱ በኋላ በተኩስ አቁም ውስጥ ሆነው ሕዝቡን ከሞት አልታደጉትም፣እዚህም እዚያም በሚቀሰቀስ ግጭት ብዙ ሕዝብ አልቋል፤ንብረት ወድሟል። ችግሩ በውይይት ያልቃል ተብሎ ሲጠበቅ የሰላም ጸር የሆኑት ወያኔና ኦሕዴድ መራሹ ብልጽግና ዳግመኛ ጦርነት ቀስቅሰዋል።በበሁለቱም በኩል የሕዝብ ድጋፍ ለማግኘት አንድ ጊዜ በእርዳታ ፣በሌላ ጊዜ በማስገደድ የዘመቻው ተካፋይ እንዲሆን የማድረጉ ቅስቀሳ በስፋት ቀጥሏል።መቀስቀስም ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የጦር ግንባሮች ጦርነት መጀመራቸውን ሁለቱም ይፋ አድርገዋል።አንዱ ሌላውን ጀመረ ሲል ቢከሰውም ሁለቱም በጦርነት የሚነግዱና ካለጦርነትም ሊኖሩ ስለማይችሉ በተለይም ሕዝብ ተማሮ ሲነሳባቸው ከዚያ የሕዝብ ቁጣ ለማምለጥና አቅጣጫውን ለመለወጥ የሚቀይሱት የሥልጣን ዕድሜ ማርዘሚያ ስልት አድርገው ለዳግመኛ እልቂት ተሰልፈዋል።በዚህም ወያኔ በቅጡ ተደራጅቶ ብዙ የሰው ማዕበል አሰልፎ በአማራውና በአፋሩ ክልል ያሉትን የቅርብ ቦታዎችን ለመቆጣጠር መቻሉ ከቦታው ሾልኮ የሚወጣው ወሬ ያረጋግጣል፣ መንግሥት ተብዬውም አምኗል። የቆቦ ከተማና አካባቢዋ የወያኔ ጦር መፈንጫ ሆናለች። መከላከያ ተብዬውም እንደልማዱ "ሕዝብ ላለማስጨረስ ስል ስልታዊ ማፈግፈግ አድጌያለሁ" በሚል ፈሊጥ ከ40 ኪሎሜትር በላይ የኋሊት ፈርጥጦ ወልዲያና አካባቢዋን ለወያኔ ጥቃት የተመቸች አድርጓታል። ወያኔ ከክልሉ ወጥቶ እንዳያጠቃ መከላከል ሲገባ ፣በነጻ እንዲገባ በሩን ከፍቶ መልቀቅ የኦሮሙማው መከላከያ የትብብር እርምጃ ለመሆኑ ሌላ ማስረጃ አያስፈልግም፤ግልጽ ነው።ያለፈውም ጊዜ እስከደብረብርሃን ድረስ የዘለቀው ወረራና ውድመት በዚህ መልኩ የተፈጸመ ክህደት ያስከተለው ውጤት ነበር።የአሁኑም ተመሳሳይ የማፈግፈግ ስልት የወሎና የአፋር ነዋሪን ሕዝብ ለወያኔ ዳግም ጥቃት አጋልጦ ሰጥቶታል።ከአንድ ዓመት ተኩል በፊት የተፈጸመው ውድመት በበለጠ ደረጃ ዳግም

መከሰቱ እንደማይቀር ሁኔታው ያመላክታል።የአፋር ሕዝብም ከአቅሙ በላይ ሆኖበት የድረሱልኝ ጥሪ በማሰማት ላይ ነው።መከላከያ ተብዬውም ሆነ የሌላው ክልል ጦር በታዛቢነት ተቀምጠዋል።የአማራው ክልል ብአዴን በሽዎች የሚቆጠሩ የአማራ ፋኖና ልዩሃይል አባላትን አስሮ ሌላው እንዲከተለው የድረሱልኝ ጥሪ አድርጓል።የማታ ማታ እንዳለፈው ጊዜ ወያኔ እዬገፋ ሲመጣ የሚችለውን ዘርፎ እንደመከላከያ ጦሩ እግሬ አውጭኝ ከማለት እንደማይመለስ ተክለሰውነቱ ያረጋግጣል።

አማራው በሰሜን ጦርነት ሲወጠር በወለጋና በሌሎቹ ቦታዎች የሚካሄደው ድምጽ አልባ ጭፍጨፋ ቀጥሏል። ከወራት ወዲህ በሽሽት ወደ አማራ ክልል የገቡት የትግራይ ተወላጆች ከለላ የሆናቸውን የቆቦ ሕዝብ ከድተው ከወያኔ ጎን ለውጊያ መሰለፋቸውና ብዙ ጉዳት ማድረሳቸው ይነገራል።ይህ እውነት ከሆነ በትግራይና በአማራ ማህበረሰብ ዘንድ የሚፈጥረው ጥላቻና አለመተማመን ቀላል አይሆንም።የትግራይ ተወላጆች ይህንን ተደጋጋሚ ጥፋት ቆም ብለው ሊያጤኑትና ከስህተታቸው ሊታቀቡ ይገባል።በተለይም በውጭ አገር የሚኖረው የከባቢው ተወላጅ ይህንን ጭፍን ጥላቻና አድራጎት ሊያወግዘውና ተጠያቂውን ወያኔን በማሶገድ ትግሉ ላይ እንዲያተኩር ለማሳሰብ እንወዳለን። በወያኔ ተመርቶ የተዋለደ ቤተሰብ መለያዬትና ልጆች ጎራ ለይተው በጠላትነት እንዲያድጉ ማድረግ ለማንም አይበጅም።ከከፋት ሁሉ የከፋ ነው።

ወያኔ የትግራይን ሕዝብ ጥያቄ ለመመለስ አቅም ሲያንሰውና ተቃውሞ እዬወለደ ሲመጣ ማምለጫው ተወረናል የሚል ታሪክ ፈጥሮ የሕዝቡን ትኩረት መለወጥና ተቃዋሚዎቹንም በመወንጀል ለማሶገድ ይጠቀምበታል።የኦሕዴድ መራሹም ቡድን እንዲሁ ሕዝቡ በኑሮ ውድነት፣በሰላም ማጣትና በህልውናው ላይ በተሰነዘረ ጥቃት ተማሮ ተቃውሞ ሲጀምር ያለው ቀላሉ ማምለጫ መንገድ ጦርነት መቀስቀስ ወይም እንዲቀሰቀስ ምክንያት መፍጠር ነው።ከሁለት ዓመት በፊት ሁለቱም አገር ጠሌ ቡድኖች የቀሰቀሱት ጦርነት ለብዙ ዜጎች ማለቅና ለአገር አቀፍ ውድመት ምክንያት ነበር፤የአሁኑም ጦርነት ከዚያ ቢከፋ እንጂ የተለዬ ውጤት አይኖረውም።ጦርነቱ እንኳን በሽምግልና ቢቆም በሕዝቡ መካከል የቋጠረው ቂም በቀላሉ የሚወገድ አይሆንም።ዘላቂ ቂምና ጥላቻ እንዳይኖር ፣ጦርነት የዘወትር ልማድ ሆኖ እንዳይቀር የጦርነት ነጋሪት ጎሻሚዎቹ ወያኔና የኦሕዴድ-ኦነግ ቡድኖች መወገድ አለባቸው።ለፈጸሙትም ወንጀል ተገቢው ቅጣት ሊሰጣቸው ይገባል።ያንን ሊያደርግ የሚችለው ሕዝቡ ነው።

በሌሎችም አገራት እንደታዬው ጦርነትን የሚያሶግደው የሕዝብ እምቢተኝነት ሲኖርና ጸረ ጦርነት ንቅናቄ ተጠናክሮ ሲካሄድ ነው።የአሜሪካ ሕዝብ በቬትናም ጦርነት ወቅት ጸረ ጦርነት እንቅስቃሴ(No War Movement) ባያካሂድ ኖሮ የቬትናም ጦርነት ሊራዘም ይችል ነበር።የሕንድም፣የደቡብ አፍሪካም ታሪክ ያንኑ ያረጋግጣል።በአገራችን ኢትዮጵያም የጦርነት ሰለባ የሆነው ሕዝብ እምቢ ጦርነት ፣የጦር ነጋሪት ጎሻሚዎችም ይወገዱ ብሎ በጋራ ካልቆመ ጦርነቱ ሊቆም አይችልም።ስለሆነም ሰላም ወዳዶቹ፣ በአንድ አገር ልጅነት የሚያምኑትና የተዋለዱ፣አብረው የኖሩና በቀጣይም ለመኖር የሚሹ፣የሁለቱንም መሰሪ ዓላማ የተረዱ ኢትዮጵያውያን በተለይም የትግራይና የአማራው ተወላጆች ግንባር ቀደሙን ሚና ሊጫወቱ ይገባል። ሰላም ወዳድ የሆነ ዜጋ የአንዱ ጎራ ተከታይና አጃቢ ሆኖ በሌላው ላይ በሚደርሰው መከራና ጥቃት ሊደሰትና ሊጨፍር አይገባውም እንላለን።የአንድ ትግራይ ተወላጅ ህይወት በከንቱ ጦርነት ሲጠፋ ለአማራውና ለሌላው ኢትዮጵያዊ ጉዳት ነው።የአማራውና የሌላው ኢትዮጵያዊም ህይወት መጥፋት እንዲሁ ለትግራዩ ተወላጅ ጥፋትና ጉዳት ነው።አንዱ በሌላው ሞትና ጉዳት የሚያተርፈው አይኖርም።በሰው ህይወት መጥፋት የሚከብሩትና የሚጠቀሙት በዬስማቸው ለጦርነት የሚቀሰቅሱት በጉልበትና በሴራ የመሪነቱን ቦታ የጨበጡት፣ዘራፊዎችና ከይሲዎች ብቻ ናቸው።

እነዚህ አገር አጥፊ ቡድኖች በአገሪቱ ሃብት የተገዛውን የመከላከያ መሣሪያ በመዝረፍና በማግረክ ተካፍለው ለጦርነት የተሰለፉ ሲሆኑ አንዱ ሌላውን እዬወነጀለ የዓለም አቀፍ ማህበረሰቡን በማወናበድ ላይ ናቸው።ወያኔ በአራት አቅጣጫ ሕጻንና ሽማግሌ፣ወጣትና አሮጊት ሳይቀር ያስገደደውን የሕዝብ መንጋ አሰልፎ በመውረር በርቀትም በሮኬትና ሚሳይልና ከባድ መሣሪያ የአማራውንና የአፋሩን ሕዝብ እዬደበደበ ለብዙዎች ማለቅና መቁሰል ምክንያት ሆኗል ፣ኦሕዴድ በበኩሉ መቀሌን በአውሮፕላን ደበደብኩ፣ጀኔራል ሳይቀር ማረኩ ይላል።ሁሉም አሸነፍኩ እንጂ ተሸነፍኩ አይልም።የሚጠቀምባት ቀዳዳ ለመፍጠር ግን ሁለቱም የተበደልኩ እሪታቸውን ያቀልጡታል።በነሱ ጫጫታ ተውጦ የሕዝቡ ድምጽ ሰሚ አላገኘም።ደጋፊዎችም ያንኑ እሪታ ተቀብለው ያስተጋባሉ።የወያኔ የመጨረሻ ግቡ የወልቃይትንና የራያን ለምና መውጫ በር የሚሆነውን መሬት መያዝና ተገንጥሎ ትግራይ የምትባል አገር መመሥረት ነው።ሱዳን፣ግብጽና ሌሎቹም የምዕራባውያን አገሮች እውቅና ይሰጡኛል የሚልም እምነት አለው።ደጋፊ የሆኑትም አገሮች ያንን ከማድረግ አይመለሱም።በሌላ በኩል ኦሕዴድ- ኦነግም በተመሳሳይ ቢቻል መላ አገሪቱን ተቆጣጥሮ ኦሮሚያ ማድረግ አለያም ተገንጥሎ የራሱን ኦሮሚያ የሚል አገር መፍጠር ነው።ለዚያም የአገሪቱን ሃብት እዬዘረፈ ተቋማትን በመገንባትና የመሬት ቅርምቱን በሰፋት እዬሄደበት ይገኛል። አዲስ አበባንም ፊንፊኔ ብሎ መሰዬሙና የከተማዋን ዳርቻ እዬዋጠ ወደመሃል የመምጣቱ ፣ የአዲስ አበባን የነዋሪ ሕዝብ ስብጥር (Demography)የመለወጡ ሂደት፣ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ አውርዶ የራሱን ባንዲራ ማንጠልጠልና በጥላቻና በውሸት ትርክት የታጨቀ መዝሙር ማዘመሩ የዚያ ማረጋገጫ ነው።

አሁን የተጀመረው ጦርነት ያለፈው ጦርነት ቅጥያ መሆኑ ሊዘነጋ አይገባም።ይህንን የወንበዴዎች ጦርነት የሕዝብ ጦርነት አድርጎ መውሰድ የወንጀለኞቹን አሻጥር አለመረዳት አለያም ተባባሪ መሆን ነው።ያለፈው ስብራት ሳይጠገን ተጨማሪ ስብራት እንዲከሰት ፈቃደኛ መሆን ወንጀለኛነትና አረመኔነትን ደግፎ መቆም ነው።በጥቅምና በሥልጣን ምክንያት የቀሰቀሱትን ጦርነት ለሕዝብ ጥቅምና ለአገር ህልውና የሚደረግ ትግል በማስመሰል ሲቀልዱበት መሳተፍ ሳይሆን ዝም ብሎ መመልከት ተጠያቂ ያደርጋል።ሰላምና እህል የናፈቀው በልቶ ያልጠገበ ሕዝብ፣እሩጦ ያልጠገበ ህጻን ፣ ተስፋ የሰነቀ ወጣት፣እርጉዝና እመጫት ሴቶች መከራ ለሚያዩበት ጦርነት መሰለፍ ጀግንነትና ብሔራዊ ክብር አይደለም።ጀግና ማለት እነዚህን ከይሲዎች ለማሶገድ የቀረጠ፣እነሱን ተከትሎ በጦር ሜዳ የተሰለፈና የገደለ ሳይሆን ጦርነትን ለማሶገድ የተሰለፈና የቻለ ነው።ሌሎቹ ጦርነትን የሚሹ ቢኖሩ የኢትዮጵያን መዳከምና መበታተን የሚፈልጉ አለያም የጦር መሣሪያቸውን ለመፈተሽ የሚሹ ነጋዴዎች ብቻ ናቸው፣በአገር ውስጥም በሕዝብ መከራ የሚነግዱና ሃብት ለመያዝ የሚስገበገቡ አረመኔዎች ብቻ ናቸው።ለነዚህ ዕድል መስጠትና በር መክፈት ከሃጢያትም በላይ ሃጢያት፣ከክህደትም በላይ ክህደት ነው።እራስን ለአረመኔዎች ጥቅም አሳልፎ መስጠት ነው።አብይም ሆነ ደብረጽዮን ፣ጻድቃንም ሆነ ብርሃኑ ጁላ ለነበራቸውና ለያዙት ወንበርና ጥቅም ሕዝብን ቀስቅሰው የሚያጋድሉ አረመኔና እራስ ወዳዶች መሆናቸውን ማወቅና ለነሱ የጦርነት ጥሪ እምቢ ብሎ መቆም ብሎም እነሱን ለማሶገድ የራሱን የተባበረ ትግል ማድረግ ዘመንና ትውልድ ተሻጋሪ ለሆነ የሚያኮራ ታሪክ ባለቤት ያደርጋል።የታሪክም ብቻ ሳይሆን የአንድና የሰላማዊ፣ብሎም ያደገች የትልቅ አገር ባለቤት ያደርጋል።

የአብይ አህመድ ኦሕዴድ ኦነግ ብልጽግና የሕዝቡን ቀልብ ለመሳብና ለማማለል፣ሰሞኑን የኢጋዴውን የጋዝ ክምችት መኖር እርግጠኛነት የሚያሳይ ሰነድ ይዞ ብቅ ብሏል።በዚህ በአሜሪካና በደቾች ተሳትፎ በተደረገ ጥናት የ7 ትሪሊዮን ጫማ ጥልቀት ያለው የጋዝ ክምችት መኖሩን በማረጋገጥ በቅርቡ ቁፋሮ ለሚጀምር ኩባንያ ጨረታ እንደሚወጣ ይፋ አድርጓል።ጨረታ ይወጣል ተባለ እንጂ ያጠኑት አገሮች ኩባንያ እንደሚወስደው እርግጠኛ ሆኖ መናገር ይቻላል።ማን ያሰባውን ከብት ማን አሳልፎ ይሰጣል?ማን ያመረተውን ሰብል ማን አጭዶስ ይወስዳል?ገና ከጅምሩ ጥናት ሲያካሂዱ የሚገቡት

ስምምነት ቢኖር ከተገኘ የሚኖራቸውን ድርሻ የሚያረጋግጥ ዋስትና መያዝ ነው።ታከለ ኡማና ልኡካኑም አሜሪካ ሄዱ ተብሎ የተነገረው ለዚያ የመጨረሻ ስምምነት እንደሚሆን መጠርጠርጠር ይቻላል።

ስለ ኦጋዴው የጋዝ ክምችት ጉዳይ ታሪክን ብናጣቅስ ገና በንጉሱ ጊዜ ተገኘ ተብሎ፣ናሙናውም በጠርሙስ ቀርቦ ታይቶ ነበር፣የውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ እንጂ!በደርግም ዘመን እራሽያኖች ፍለጋውን አካሂደው መኖሩን አረጋግጠው ነበር፤በወያኔ ጊዜም ቻይናዎች ተረክበው ማውጣት እንደጀመሩ ተነግሮ ነበር።በቻይናዎች ያልተደሰቱት ምዕራባውያን የሶማሌ ነጻ አውጭ ነኝ የሚለውን ቡድን አደራጅተው በቻይናዎች ላይ ጥቃት እንዲፈጸም ተደርጎ 30 ቻይናዎች ከተገደሉ በኋላ ሥራው ቆመ።የእንግሊዝ መንግሥትም እርምጃ የወሰዱትን በፊት አሸባሪ ብሎ የሰየማቸውን የኦጋዴ ነጻ አውጭ ቡድኖችን ለዴሞክራሲ የሚታገሉ ብሎ እውቅና ሰጣቸው፣ከዓለም አቀፍ የሽብርተኞች ተራም አወጣቸው፣በአገሩ ለገቡት የድርጅቱ ደጋፊ ለሆኑት ስደተኞችም የመኖሪያ ፈቃድ አደላቸው።ለምዕራባውያን ጥቅም የቆመ ሁሉ ዴሞክራት ነው፤የነሱ ተቃዋሚና አገር ወዳድ የሆነ ደግሞ አሸባሪ ይባላል።

የአሁኑ የጋዝ ክምችት ቢወጣ ከጥቅሙ ጉዳቱ የሚያመዝንና ይዞት የሚመጣው የበለጠ ቀውስ እንደሚሆን መዘንጋት የለበትም።የሰፈነው የጎሳ ፖለቲካ ባመጣው ጣጣ መሬት የእርስ በርስ ግጭት ምክንያት በሆነበት አገር እንደዚህ አይነቱ ትልቅ የተፈጥሮ ሃብት ለአንድነት፣ለሰላምና ለጋራ ጥቅም ይውላል ብሎ መገመትና ማሰብ የዋህነት ነው።ሕዝብ በጎሳ ማንነቱ  አገርህ አይደለም እዬተባለ በሚጨፈጨፍበትና በሚፈናቀልበት አገር ውስጥ ሆኖ ከሚኖርበት አካባቢ ውጭ ያለው የተፈጥሮ ሃብት የእኔም ነው ብሎ የመቁጠርና የመኩራት ስሜት ሊኖረው አይችልም።  “ፊት አባት ይኑርሽ በኋላ ማይበት” እንደሚባለው ከሁሉም መጀመሪያ ሕዝቡ ያገሩ ባለቤት ይሁን ከዚያም በአገሩ ውስጥ ያለውን የተፈጥሮ ጸጋ ሊያዝበት ይችላል።ያ በሌለበት  እዚህ ቦታ ነዳጅ፣እዚያ ቦታ ወርቅ፣እዚህ ቦታ ኡራኒዬም እዚያ ቦታ ፖታሽ፣እዚህ ቦታ ብረት ፣እዚያ ቦታ ግድብ ቢሉት “ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ” ከሚለው ብሂል የራቀ ምኞትና ተስፋ የሰነቀ ብሔራዊ ንብረት አይሆንም። በአገሩ ውስጥ ያለውን የተፈጥሮ ጸጋ ሊያዝበት የሚችለው ጦርነትን ተቃውሞ ጦረኞችን ፤የግጭት ምክንያት የሆነውን የጎሳ ፖለቲካንና ጎሰኞችን ከነአስተሳሰባቸው ሲያሶግድና ኢትዮጵያን በጠንካራ ማማ ላይ ሲያቆማት ብቻ ነው።

በውጭ አገር የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ፣የትግራይ፣የአማራውና የሌላው ማህበረሰብ ተወላጅ የጦርነቱን ወሬ ከማናፈስና ወገን ለይቶ ግፋበት ከማለት እራሱን የሰላም ወታደር እንዲያደርገው ጥሪ እናስተላልፋለን።ምሁሩም በዬመድረኩና አዳራሹ ጉንጭ አልፋ ውይይት ከማድረግ ወጥቶ ለሰላሙ ንቅናቄ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ለማሳሰብ እንወዳለን።ሰላም ስንል ከጦርነት  ቀስቃሾች ጋር መሞዳሞድና እራሱን ለሹመት ማቅረብ  ሳይሆን ጸረ ጎሰኞች ፣ጸረ ህወሃት፣ጸረ ኦነግ-ኦሕዴድ የሆነ ኢትዮጵያዊነትን ያንጸባረቀ ሕዝባዊ ንቅናቄ ማለታችን እንደሆነ ይሰመርበት።ለዚያ ፋና ወጊ የሚሆነው የአማራውና የጉራጌው እንዲሁም ሌላው ማህበረሰብ የሚያካሂደውን የተናጠል ትግል በአንድ ላይ ማስተሳሰርና ብሔራዊ መልክ እንዲይዝ ማድረግ ነው።በሁሉም ማህበረሰቦች ላይ የሚደርሰውን መከራ ለመቋቋም ብሎም ለማሶገድ የሚችሉት ትግላቸውን አንድ ላይ የሚያስተባብር የጋራ አካል መፍጠር ሲችሉ ነው።ሕዝቡንም በጸረ ጦርነት ንቅናቄ ውስጥ እንዲገባ ሲቀሰቅሱት ነው።

ጦርነት አውዳሚ ነው!የጦርነት ነጋሪት ይቀደድ!!ጦረኞችም ይወገዱ!!!

ጸረ ጦርነት ሕዝባዊ  ንቅናቄ ይጀመር!!

ኢትዮጵያ በሰላምና በነጻነት ለዘለዓለም ትኑር